| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ድርሰት ። |
| ርእስ ፤ | "የኢትዮጵያ ፡ ፋኖ ። " |
| ደራሲ ፤ | አውሳቤ ፡ ነጋ ። |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 2018 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2018-003 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | (የግል ፡ አስተያየት ። ) |

## ድርሰት

Essay | Essai | مقال

# የኢትዮጵያ ፡ ፋኖ ።

አውሳቤ ፡ ነጋ ።

ዐማራ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሠራ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ በባህሉ ፡ እና ፡ በቋንቋው ፡ አንድ ፡ ያደረገ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አካል ፡ ነው ። እንደ ፡ መኾኑም ፥ ኢትዮጵያን ፡ አድክመው ፡ ለመቀራመት ፡ ያቀዱ ፡ የአውሮፓ ፡ አገሮች ፡ ዋና ፡ ጠላት ፡ አድርገው ፡ ሊያጠፉት ፡ ወሰኑ ። ይህ ፥ የታወቀ ፡ ዕቅዳቸው ፥ "አልገዛም!" ፡ ባዩን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሲፈትነው ፡ ኖሯል ። ፋሺስት ፡ ኢጣልያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ስትወር ፥ ዐማራውን ፡ ለይታ ፡ ለማጥፋት ፡ ብትሞክርም ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ መክቶ ፡ መልሷታል ። አንድነቱ ፡ እንዳለ ፡ ኖሯል ።

የዛሬ ፡ 34 ፡ ዓመት ፥ ለዐማራ ፡ እና ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ጥፋት ፡ በነጻ ፡ አውጪነት ፡ ሽፋን ፡ የተመለመሉት ፥ ያገሪቷን ፡ በትረ ፡ ሥልጣን [1] ፡ ከሌላ ፡ ወንበዴ ፡ ተረክበው ፡ አንዴ ፡ ለመቼም ፡ ዐማራን ፡ አጥፍተው ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለጌቶቻቸው ፡ ለማስረከብ ፡ ሲሞክሩ ፥ ለዋናው ፡ ተልእኳቸው ፡ መሳካት ፥ ኢትዮጵያውያንን ፡ በ"ዘር" ፡ (በ"ብሔር" [2]) ፡ ከፋፍሎ ፡ ለማድከም ፡ በሚዛቀቍበት ፡ ጊዜ ፥ "ዘሩ"ን ፡ ሲጠይቁት ፥ ዐማራው ፡— «ዐማራነቴ ፡ የግሌ ፡ ነው ፥ ምን ፡ አገባኽ ! ኢትዮጵያዊ ፡ ነኝ ! » ፡ ይል ፡ ነበር ። የዐማራነት ፡ መንፈስ ፡ ይህ ፡ ነበር ። ዐማራነት ፡ መንፈስ ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ በዚህ ፡ አልተሳሳቱም ።

1 ያገሪቷን ፡ መንግሥታዊ ፡ ኀይል ። [አዘጋጅ]

2 በመሠረቱ ፥ "ብሔር" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የሚያመለክተው ፡ የቦታ ፡ ስፋትኝ ፡ እንጂ ፡ ማኅበረሰብን ፡ አይደለም ። ሲጠብ ፡ ምድርን ፡ (territory • territoire) ፥ ሲሰፋ ፡ ደግሞ ፡ መላው ፡ ዓለምን ፡ እና ፡ ጠፈርን ፡ (universe • univers) ፡ ያመለክታል ። [አዘጋጅ]

ዛሬ ፡ የምናየው ፡ ምንድነው ? የዛሬ ፡ 7 ፡ ዓመት ፡ "አሮም ፡ ነን" ፡ ባይ ፡ ወሮበሎች ፡ በትረ ፡ ሥልጣኑን ፡ ከግብር ፡ ዐበሮቻቸው ፡ ተረክበው ፥ የጋራ ፡ ዐላማቸውን ፡ እፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፥ ባረመኔ ፡ መንፈስ ፡ ዐማራ ፡ ላይ ፡ ሲነሡ ፡— «ዐማራ ፡ የህልውና ፡ አደጋ ፡ አለበት ፤ ስለዚህ ፡ መልሱ ፡ ከዐማራ ፡ ነው ፡ የሚመጣው» ፡ የሚሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ የሕዝቡን ፡ ትግል ፡— «የዐማራ ፡ ትግል ፡ ነው ፤ የጠፋው ፡ ዐማራ ፡ ነው ፤ አጥፊዎቹ ፡ ደግሞ ፡ "ኢተዮጵያውያን ፡ ነን" ፡ የሚሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ የሚሠሩ ፡ ናቸው» ፡ በማለት ፡ ትግላቸውን ፡ በዐማራ ፡ ትግለነት ፡ ወስነውት ፥ የዐማራ ፡ ፋኖን ፡ መሠረቱ ። (በኢተዮጵያ ፡ ታሪክ ፥ ፋኖ ፥ ሥርዐት ፡ ሲፈርስ ፡ አገርን ፡ የሚታደግ ፡ ሕዝባዊ ፡ ኀይል ፡ ነው ። ዛሬ ፡ አነሣሡ ፡ በመሠረቱ ፡ ያው ፡ ቢኾንም ፥ ከመነሻው ፡ ወደ ፡ ዐማራ ፡ ትግልነት ፡ ብቻ ፡ እንዲያመራ ፡ ተደርጓል ። )

የዛሬ ፡ 90 ፡ ዓመት ፥ ጣልያን ፡ ኢትዮጵያን ፡ በወረረችበት ፡ ጊዜ ፥ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሲሰደዱ ፥ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዐርበኛ ፡ (ፋኖ) ፡ ተነሥቶ ፡ አገሩን ፡ አዳነ ። ጣልያን ፥ ያስቸገረውን ፡ ዐማራን ፡ ለይቶ ፡ ለመምታት ፡ ያደረገው ፡ የ"ዘር" ፡ መለየት ፡ ሙከራ ፡ ፈጽሞ ፡ ተከታይ ፡ አላገኘም ። ኢትዮጵያ ፡ ብሎ ፡ የተነሣው ፡ ዐርበኛ ፡ ኢትዮጵያን ፡ አዳነ ። እንዲሁም ፡ የዛሬ ፡ 130 ፡ ዓመት ፡ የጣልያንን ፡ ጦር ፡ አደባይቶ ፡ የመለሰው ፡ መላው ፡ የአትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ።

"የዐማራ ፡ ፈኖ" ፡ ሲባል ፡ ሌላውን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ያካትታል ፡ ወይ ? የፋኖ ፡ መሪዎች ፡ ሲጠየቁ ፤ « ትግሉ ፡ የዐማራን ፡ ህልውና ፡ ለማዳን ፡ የተዠመረ ፥ ሌላውን ፡ ያላካተተ ፥ የዐማራ ፡ ብቻ ፡ ትግል ፡ ነው ። አሸንፈን ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ("አራት ፡ ኪሎ") ፡ ስንገባ ፡ ከሌሎች ፡ "ብሔሮች" ፡ ጋራ ፡ እንመክራለን » ፡ የሚል ፡ አስደንጋጭ ፡ መልስ ፡ ይሰጣሉ ። ከቶ ፡ "ሌሎች ፡ ብሔሮች" ፡ ማለት ፡ ትርጕሙ ፡ ምንድነው ? የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድ ፡ ሳለ ፡ በ"ብሔር" ፡ ከፋፍሎ ፡ መናገር ፡ ጥቅሙ ፡ ምን ፡ ላይ ፡ ነው ? ኢትዮጵያውያን ፥ መለስ ፡ ዜናዊ ፡ በወሰነላቸው ፡ አጥፌ ፤ የባንዳ ፡ ተልእኮን ፡ ባዘለ ፡ በ"ዘር" ፡ ከፋፋይ ፡ ሥርዐት ፡ ይቀጥላሉ ፡ ብሎ ፡ የሚያስብስ ፡ ማን ፡ ነው ? ይህ ፡ የሚያመለክተው ፡ የፋኖን ፡ ትግል ፡ በዐማራ ፡ መወሰን ፡ ያዘለውን ፡ ለጊዜው ፡ ለብዙዎች ፡ የማይታይ ፡ ከባድ ፡ ችግርን ፡ ነው ። ይህ ፡ አንሶ ፥ በእየቦታው ፡ «ዐማራ ፡ ነን !» ፡ የሚሉ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ስም ፡ ሲነሣ ፤ « ኢትዮጵያ ፡ "ዐማራ" ፡ ብላ ፡ እየገደለችን ፡ ምን ፡ ታደርግልናለች ? ዐማራ ፡ ያልኾንክ ፡ ባማራ ፡ ጕዳይ ፡ አትግባ !» ፡ እያሉ ፡ ሌላውን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ገለል ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2018 ፡ ዓ.ም. ።

እንዲል ፡ በማድረግ ፥ ትግሉ ፡ እንዲጓተት ፡ እና ፡ ፍጻሜው ፡ የዘረኝነት ፡ በሽታ ፡ ያዘለ ፡ እንዲኾን ፡ ተግተው ፡ ይሠራሉ ። ከባንዳ ፡ አሠራር ፡ በምንም ፡ አይለይም ። ይህ ፡ አስተሳሰብ ፡ በመደበኛው ፡ ፋኖ ፡ ዘንድ ፡ የሌለ ፥ በተወሰኑ ፡ "መሪዎች" ፡ ዘንድ ፡ የሚታይ ፥ ተነቅሎ ፡ መጣል ፡ ያለበት ፡ ዐረም ፡ ነው ።

ዐላማቸውን ፡ ሲጠየቁ ፡ ደግሞ ፥ « ዐማራ ፡ የሚከበርባትን ፡ ኢትዮጵያ ፡ መገንባት ፡ ነው !» ፡ የሚል ፡ አኹንም ፡ አስደንጋጪ ፡ መልስ ፡ ያስሰማሉ ። ይህ ፥ የሠለጠነ ፡ ሕዝብ ፡ መንግሥት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አለመረዳት ፡ ነው ። ኹሉም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሊመኝ ፡ የሚገባው ፥ የሚመኘውም ፥ ሰው ፡ እንደሰው ፡ ልጅነቱ ፡ ተከብሮ ፡ በሕግ ፡ እኩል ፡ ኾኖ ፡ የሚኖርባትን ፡ አገር ፡ ነው ። በሕግ ፡ ረገድ ፡ ዐማራ [3] ፥ ሶማሌ ፣ ትግሬ ፣ ኦሮሞ ፣ ወዘተ... ፡ የሚባል ፡ አካል ፡ የለም ። አለዚያ ፡ ተመልሶ ፡ አገር ፡ ለማጥፋት ፡ የታወጀው ፡ "የብሔር ፡ እኩልነት" ፡ የሚሉት ፡ ደግ ፡ መስሎ ፡ አጥፊ ፡ ሐሳብ ፡ ያመጣውን ፡ የ"ዘር" ፡ መለያየት ፡ ዳግም ፡ ተሸክሞ ፥ «ምን ፡ ይኾን ፡ ይችን ፡ አገር ፡ ከመከራ ፡ እንዳትወጣ ፡ ያደረጋት?» ፡ እያሉ ፡ ባላዋቂነት ፡ እያላዘኑ ፥ ከድጡ ፡ ወደ ፡ ማጡ ፡ መውረድ ፡ ይኾናል ። ለዚህ ፡ ችግር ፥ እኩሉ ፡ ሰው ፡ እና ፡ በሰው ፡ እንጂ ፡ "ብሔር" ፡ እና ፡ "ብሔር" ፡ አለመኾኑን ፡ መረዳት ፡ አንድያው ፡ መፍትሔ ፡ ነው ።

ኢትዮጵያን ፡ ሊያጠፉ ፡ የተመደቡ ፡ ወሮ ፡ በሎችን ፡ አግልሎ ፡ አገሪቷን ፡ ለማዳን ፡ ፋኖ ፡ ወደ ፡ አገራዊ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዐርበኛነቱ ፡ ተመልሶ ፥ የያዘው ፡ ሰንደቅ ፡ ዐላማ ፡ እና ፡ የተሰየመባቸው ፡ ለትውልድ ፡ "ኢትዮጵያን ፡ ዐደራ" ፡ ብለው ፡ ላገራቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሞቱ ፡ ዠግኖች ፡ እንደሚመሰክሩለት ፥ ራሱን ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ፋኖ" ፡ ብሎ ፡ ትግሉን ፡ እዳር ፡ ማድረስ ፡ ይጠበቅበታል [4] ❖

---

3 ዐምሐራማ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ በ"ብሔሮች" ፡ ተርታ ፡ አይኰለኰልም ። ኢትዮጵያን ፡ በኢምፔሪያሊስቶች ፡ ዐቅድ ፡ በ"ብሔር-ብሔረሰብ" ፡ አዋቀርን ፡ ያሉ ፡ ኀይሎችም ፡ ቢኾኑ ፥ «ዐማራ ፡ የሚባል ፡ ብሔር ፡ የለም!» ፡ በሚል ፡ ከሕገ ፡ ውንብድናቸውም ፡ ቀረጻ ፡ አላሳተፉት ። [አዘጋጅ]

4 **ዐምሐራ** ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብ ፡ (citizenry • peuple citoyen) ፡ የኾነውን ፡ ያኽል ፡ "የዐምሐራ ፡ ፋኖ" ፡ ተብሎ ፡ መሰመዩ ፡ ስሕተት ፡ አይኾንም ። ጥፋት ፡ የሚኾነው ፥ ያልኾነውን ፥ «ዐምሐራ ፡ "ዘር" ፡ ነው!» ብሎ ፡ ፋኖን ፡ በ"ዘር" ፡ ለማደራጀት ፡ መሞከር ፡ ነው ። የዐምሐራን ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብነት ፡ መካድ ፥ ኢምፔሪያሊዝም ፡ ራሱ ፡ የሚመራው ፥ ኢትዮጵያን ፡ አስቀድሞ ፡ ባለቤት-አልባ ፡ የማድረግ ፥ ቀጥሎም ፡ የማፈራረስ ፡ ዐቅድ ፡ መኾኑ ፡ ታውቋል ። "የኢትዮጵያ ፡ ፋኖ" ፡ ማለቱ ፡ የሚደገፍበት ፡ ዋነኛ ፡ ምክንያት ፥ የ 50 ፡ ዓመቱ ፡ የተሳሳተ ፡ ስብከት ፡ ትውልዱን ፡ ስላደናገረው ፥ ዛሬ ፡ ኹሉን ፡ በሚያስማማ ፡ አጠራር ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ፋኖ" ፡ ብሎ ፡ መጥራቱ ፡ የተሻለ ፡ ስልት ፡ ስለሚመስል ፡ ነው ። ለዘለቄታው ፡ ግን ፥ ዐምሐራነት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሕዝብነት ፡ የማይወጣ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ "የዐምሐራ ፡ ፋኖ" ፡ ማለቱ ፡ ከጕዳቱ ፡ ይልቅ ፡ ጥቅሙ ፡ ያመዝናል ፡ ቢባል ፡ ስሕተት ፡ አይኾንም ። [አዘጋጅ]


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2018 ፡ ዓ.ም. ።